# ብላቴና የግፉአኑ ብሩህ ተስፋዎችና

# ስጋት የወለደው የስደተኛ ወላጆች ህብረት !

ሾተል-ከባህረ ሰላጤ

በሳውዲ አረቢያ ፤ በተባበሩት አረብ ኢምሬት ፣ በዱባይ ፤ በአቡዳቢ፤በሻርጃ ፤ በቃጣር ተበትነናል፡፡ ብዙዎቻችን ኑሮው የአሳር የፍዳ መሆኑን እያወቅንና እየሰማን የስራ እጦት ገፍትሮ ከቀያችን ያስዎጣን ነን ከማለት ይልቅ የኑሮ ውድነት አስመርሮ ያሰደደን በኢኮኖሚ ስደተኛ ነን ማለቱ ይቀል ይመስለኛል፡፡ የዚህ መጣጥፍ ዋንኛ ትኩረቴ ወደ አረብ ሃገራት " የተስፋ ምድር" ለስኬት በበቃንና በህጋዊነት ስለከተምነው ኢትዮጵያዊያን ውሎ አዳር ይሆናል፡፡ የዛሬ ትኩረት አቅጣጫየ ስለ ብላቴና ልጆቻችን ብሩህ ተስፋዎችና ስጋት ስለወለደው የወላጆች ህብረት ጥቂት ለማለት ነው፡፡



ት/ቤት

ከሃገር ውጭ ከሚገኙ የኢትዮጵያ አለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች መካከል ሳውዲ አረቢያ ሪያድና ጅዳ የሚገኙት ትምህርት ቤቶች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ በምኖርበት በጂዳ አካባቢ አቅም ሳይፈቅድላቸው ቀርቶ እቤት የሚውሉትን በሺዎች የሚቆጠሩ ታዳጊ ህጻናት ይገኛሉ፡፡ በአንጻሩ አቅም የፈቀደላቸው 1,950 ተማሪዎች ባሁኑ ሰአት በኢትዮጵያ አለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች ይማራሉ፡፡

በእነዚህ ታዳጊዎች ላይ የምናየው ተስፋም አስደሳች ነው፡፡ ከቅርብ አመታት ወዲህ ትምህርት ቤቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የመልቀቂያ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይህም በመሆኑ ዛሬ በርካታዎች ባመጡት ውጤት ሃገር ቤት በሚገኙ የተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ገብተው ለከፍተኛ ማዕረግ የሚያበቃ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ናቸው፡፡

በውጭ ሃገር ተወልደውና አድገው ለዚህ መሰሉ ወግና ማዕረግ ሲበቁ ማየት እሰየው ነው፡፡ ያለመታደል በሉት መታደል ተወልደው ያደጉት በአረብ ሃገር ነውና በአውሮፓና አሜሪካ ያደጉ የኢትዮጵያውያን ልጆች ያላቸውን ያህል ሰፊ የመማር እድል ባይኖራቸውም ወላጆች በጠባቡ መንገድ ተጉዘን ልጆቻችን ለዚህ ሲበቁ ማየት የሚሰጠው ደስታ በቃላት አይገለጽም፡፡ ልጆቻችን ከወንድሞቻቸው ጋር በአንድነት፤ በራሳቸው መምህራን በቋንቋቸውና በባንዴራቸው ስር በፍቅር ትምህርትን ቀስመዋልና ሃገር ቤት ሲገቡ ላልተወለዱበትና ላላደጉበት ሃገር ባዳ አይሆኑም፡፡ ሌላው ቀርቶ አማርኛን አቀላጥፈው መናገራቸውና ሃገር ቤት ሲሄዱ ከዘመድ አዝማድ ከወገኑ እንደፈለጉ ይጫወታሉ፡፡ በወግ አድገዋልና አክብሮት ኩራት ይሉኝታው ውበት ሁኗቸው ግንኙነታቸውን ያጎለብተዋል፡፡ ይህንን ከራሴ ገጠመኝ ጋር እያውሳሁ መጫዎቱ ያግባባን ይመስለኛል፡፡ አሜሪካና አውሮፓ የሚኖሩ እህትና ወንድሞቹ ልጆች የሰማንያ አመት ባለጸጋ እማሆይ እናቴን አያታቸውን ካንድም ሁለት ሶስቴ ሊጠይቋዋት ቢመጡም በልጅ ልጅ እና በአያት መካከል የታዘብኩት ያለመግባባት ከአእምሮየ አይጠፋም፡፡

pdfMachine
A pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ያጎት ያከስት የአያትና የልጅ ልጅ ጣፋጭ ግንኙነት እንደ ዱዳ በጥቅሻ ለመግባባት ሲሞከር … እያወለጋገዱ እንግሊዝኛውን ለሚናገሩት አስተርጓሚዎች በኩል እንኳ መግባባቱ አልሰምር ሲል… የአባት የናቶቻቸውን እድገት ታሪክ ነጋሪ የሆነችው የልጆች አያት ለዛ ያለው እናታዊ ምክር ሳይሰማ ሲቀር … አያትና የልጅ ልጅ ተረቱ ቀርቶ "በሞቴ አፈር ስሆን …ይህችን ብላልኝ…" የሚለው የእናት አለም ዳረንነት ጉርሻ ግልግል በመግባቢያ ቋንቋ ተገድቦ ሲቀር … ለመግባባት መቁለጭለጭ በእጅ ምልክት መጠቆሙን ሲሞክሩ ሳይሳካላቸው የከረሙበትን አጋጣሚ ደጋግሜ ተመልክቻለሁ፡፡ አድማስ ባህር ሊጠይቋት ከመጣች አያት ጋር ቢገናኙም ከቤት ውለው ሲያድሩ ያለ አባትና እናቶቻቸው ድልድይ ሳይግባቡ መሰነባበታቸው የሚዘነጋኝ አይደለም፡፡ እኔም ከዚህ ብዙ መማሬ ይገባኛል፡፡ ያኔ ታዝሎ ለነበረው ልጄ ትምህርት መጻኤ ህይዎት እውቀት የቀሰምኩበት ጥሩ አጋጣሚ ነበር ማለት እችላለሁ፡፡ ያም ሆነና ዛሬ ዘጠኝ አመቱን ጥር ሲገባ የሚደፍነው ብላቴና ልጄ እንደ አጎትና አክስቱ ልጆች ግራ እንደማይጋባ ግን እርግጠኛ ነኝ፡፡ በዚሁ ትምህርት ቤት የሚማሩ ታዳጊዎች በሃገራቸው ባህልና የትምህርት ስርአት አማርኛን ጭምር ተምረዋልና ሶስት ቋንቋን አቀላጥፈው (አማርኛ አረብኛና እንግሊዝኛን) ይናገራሉ ይጽፋሉ፡፡ ሃገር ቤት ለእረፍት ሲሄዱ እንደ አሜሪካና እንግሊዝ የወንድንም እህቶቸ ልጆች አይሸማቀቁም፡፡ አንዳንዴማ የሚያጫውታቸው ዘመድ ካገኙ አለያም ከጎረቤት ልጆች ጋር ሲጨዋወቱ ይውሉና የምንገናኘው ጀንበር ሲጠልቅ ነው፡፡ የመግባባት ብሎ ችግር የለም፡፡ ከአያታቸው ጉያ ተወሽቀው እኔን ካሳደገኝ ከኔ እማማ አለንጋ ጣት እየጎረሱ የኔኑ ውልደትና እድገት አፋቸውን ከፍተው በተመስጦ ይሰማሉ፡፡ ደጓ አያትም የልጅ ልጆቿን እቅፍና ድግፍ እያደረገች ጸጉራቸውን በማሻሸት የእናትነት ፍቅርዋን በተረት ተረት እያጀበች ነዲድ ፍቅሯን ታወርሳቸዋለች፡፡ እህት ወንድም ዘመድ አዝማድ ጎረቤቱን ያለ አስተርጓሚ እንደፈለጉ ያወጓቸዋል፡፡ ገጠር ወጣ ብለን ባድማ ቀየውን ስንጎበኝ ከከብት ጠባቂ ያከስት ያጎቴ ልጆች ጋር ወንዝ ድረስ እየሄዱ ተጫውተው ውለው ይመለሳሉ፡፡ ይህን መሰሉን ጸጋ ደጋግሜ ታድየዋለሁ…ተመልክቸዋለሁ፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው ግን ልጆች በባህላቸውና በቋንቋቸው የሚማሩበት ትምህርት ቤት የመማር እድልን ስላገኙ መሆኑን በልበ ሙሉነት መናገር እችላለሁ፡፡

ወደ ጅዳ አለም አቀፍ ት/ቤት ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ስንመለስ ት/ቤቱ ተማሪ የመቀበል አቅሙ ሰፍቷል፡፡ አቅም የሌላቸው ወላጆችን በመደገፍ ከ30 ላላነሱት ተማሪዎች የነጻ ትምህርት ይሰጣል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ከ130 ለማያንሱ አብዛኛው ኢትዮጵያውያን ሰራተኞች የስራ እድልን የተገኘውም በትምህርት ቤቱ ነው፡፡ በደፈናው ትልቅ የትምህርት ማዕከልም ሆኗል፡፡

ልክ የዛሬ አስራ አንድ አመት ገደማ ትምህርት ቤቱ ገና ዳዴ ሲል ተስፋውን አሻግረው ያዩት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዲፕሎማት የሰጡኝ ቃል ወደ ኋላ የማዘክረው ሲሆን የትንበያቸው እውነትነት የተረዳሁት የትምህርት ቤቱን እንቅስቃሴ በቅርብ መከታተል ስጀምር ብቻ ነበር ማለት እችላለሁ፡፡ በታዳጊ ተማሪዎች ዙሪያም ቢሆን ጠጋ እያልኩ አንዳንድ ሁኔታዎችን ለመመልከት መሞከሬ አልቀረም፡፡ በተለይም በዚህ አመት ለከፍተኛ ትምህርት ያለፉ 17 ያህል ወጣቶች በዘመን አመጣሹ የኢንተርኔት መረብ አማካኝነት ተወዳጅ በሆነው የ Facewbook ማህበራዊ ትሥሥር መረብ አባል መሆናቸውን ተረዳሁ፡፡ ታዳጊዎች መለያቸውን በጂዳ ሳውዲ አረቢያ የኢትዮጵያ አለም አቀፍ ት/ቤት የሚል ስም እንደሰጡት ሰምች ነበርና ጥያቄ አቅርቤ ተፈቅዶልኝ አባል ከዚያም ወደ አስተዳደሩ ለመግባት ቻልኩ፡፡ በአጠቃላይ ከዚያ ጊዜ አንስቶ የታዘብኩት የተስፋው ቃል እውን እየሆነ መምጣቱን ነበር፡፡ የሚጽፉዋቸው ጽሁፎችና

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የሚያቀርቡት ሃሳብና የሚናገሩትን ስመለከት ደስታየ ወሰን ያጣል፡፡ ከሃገሬው የማይተናነስ ጸዳ ያለ አረብኛና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎትና እሳቤያቸውን ከሚያቀርቡዋቸው የመወያያ ርእሶችና ከሚሰጡዋቸው አስተያየቶች ተነስቸ ስገመግመው "የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል " እንድል አስገድዶኛል፡፡ በእርግጥም እኒህ ታዳጊዎች ሃገር ተረካቢ ወጣቶች የሚጎመሩ ተስፋችን ስለመሆናቸው የመጨረሻው የሚያውቀው ፈጣሪ ቢሆንም እንደሰው እንገምት ከተባለ ተስፋ ስለመኖሩ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል ፡፡ ታዳጊዎች በአረቡ አለም አለምና በሃገራችን መካከል በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የሚታየውን ክፍተትም ሆነ የሙብት ጥበቃ በአግባቡ ሊወጡ የሚችሉ ለመሆናቸው ልቤን ልብ ሰጥተውታልና በዳግም ተስፋ ደስታየ ወሰን አጣ !

ይህ ሁሉ ሲባል ትምህርት ቤቱን በባለቤትነት የሚያስተዳድረው የጅዳና አካባቢው መስሪያ ቤት የሚመራው በበጎ ፈቃደኝነት በመሆኑ በርካታ ችግሮች እንደሚስተዋሉ መካድ አይቻልም፡፡ ያም ሆኖ ግን ብዙዎቻችን በኮሚኒቲው ስር አለ የሚባለውን የፖለቲካ ቡጢ እየፈራን በመራቃችንና በራሳቸን ቤት የሩቅ ተመልካች ሆነን ከርመናል፡፡ ትምህርት ቤቱን በማንቀሳቀስ ረገድ ችግሩ እያንገጫገጨውም ቢሆን ኮሚኒቲው እዚህ የደረሰበት ጉዞ የሚደነቅ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ኮሚኒቲው በአሁኑ ሰአት መጠነ ሰፊ በሆነ  ውስጣዊ ችግሮች ተወጥሯል፡፡ የመንግስት ተወካይ ዲፕሎማቶች ትልቁን ስራ ሊሰራ የሚችለውን ኮሚኒቲ ከማደራጀት ይልቅ ትኩረታቸው የፖለቲካና የዘር የልማት ማህበራትን ከማደራጀት የወጣ ስራ ሲሰሩ አይታዩም፡፡ አምባሳደራችን በቅርቡ ከ15 አመት ግልጋሎት በኋላ ስንብት ሲያደርጉ ለስኬታቸው ደጋግመው የሚያነሱት የትምህርት ቤት ምስረታ መሆኑ ቅር አያሰኘንም፡፡ ሆኖም ትምህርት ቤቱ እንደተፈለገ ድጋፍ አግኝቶ የፖለቲካ ድርጅቶችንና የልማት ማህበራትን ያህል ድጋፍ አላገኘም፡፡ ከዚህ ባለፈ ከክትትልና ጉድለት አሁን የትምህርት ቤቱ ባለቤት ኮሚኒቲና ትምህርት ቤቱ ያሉበትን ደረጃ የሚያውቁት አይመስለኛም፡፡ ኮሚኒቲውን ለማደራጀትና ትምህርት ቤቱ የራሱ ህንጻ እንዲኖረው ለማድረግ የተደረጉት ጥረቶች አለመሳካት ፤በአሁኑ ሰአት እየተደረገ ያለ ጥረት አለመኖር በራሱ በትምህርት ቤቱ እድገት ላይ አሉታዊ ስሜት መፍጠራቸውን መካድ አይቻልም፡፡ ይህ በመሆኑ የትምህርት ቤቱ ባለቤት ኮሚኒቲም ሆነ ትምህርት ቤቱ ተዳክሟል ከሚል መደምደሚያ የደረሱ ወላጆች በርካታዎች ናቸው፡ ኮሚኒቲው ከ21 የምክር ቤት አባላት መካከል ተመናምነው የቀሩት ከ8 ያልበለጡ ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቱን አጣብቂኝ ውስጥ የሚያስገቡ ከፍተኛ ወጭዎች ያለበቂ ጥናት በጥቂት የምክር ቤት አባላት ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡ የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅ የመማሪያ መሳሪያዎች ይቅረቡ ፤ የመምህራን ቅጥር ይደረግ፤ የደመወዝ ማሻሻያ በጥናት ይሰራ፤ የላቡራቶሪ መሳሪያዎች ይገዙ፤ በሚል መምህራን ሲጠይቁ ምላሹ አጥጋቢ ያልሆነ መልስ እነደሆነ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡ ከዚህ አልፎ ተርፎ ተስፋ በጣልንበት ትምህርት ቤት የመምህር እጥረትና የትምህርት ጥራት እያሽቆለቆለ በመጣበት በዚህ ወቅት ያለ እቅድና ፕሮግራም በሌለ ባጀት ማመላለሻ አውቶቡሶች ሲገዙ መክረሙ ለብዙዎች ስጋት ፈጥሮዋል፡፡ ትምህርት ቤቱ ዘገምተኛ ጉዞ ይጓዛል የሚለውን ሂስ በክፍል ማስፋፋትና በተማሪ ቅበላው ማሳደግ መፍትሄ ይገኝ ይመስል እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ትምህርት ቤቱ አጣብቂኝ ውስጥ ለመግባቱ በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡ ይህም ወላጆች ወደ ትምህርት ቤቱ ትኩረታቸውን እንዲያደርጉ ትኩረት ስቧል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ ወላጆች ስለልጆቻቸውና ስለትምህርት ቤቱ ሃሳብና ቅሬታቸውን የሚያቀርቡበት መንገድ የተዘጋ ነው፡፡ በትምህርት ቤቱ በተማሪዎች መካከል ድልድይ መሆን የሚገባው የወላጇ ኮሚቴ ከአመት በላይ ስራውን መስራት ሲሳነውና

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ችግሮች ሲበራከቱ የመንግስት ተወካዮችና የኮሚኒቲ ሃላፊዎች ዝምታን መምረጣቸው ለወላጁ የእግር ላይ እሳት ሆኖበት ቢከርምም የሚናገር ጠፍቷል፡፡

ይህ መሰሉ መሰራታዊ ችግር ያሳሰባቸው ከሃያ የማይበልጡ ወላጆች በወርሃ ህዳር መገባደጃ ስብሰባ ለመጥራት ይቻል ዘንድ ወኪሎቻቸውን ወደ ኮሚኒቲው ላኩ፡፡ ይህ ጥያቄ ለኮሚኒቲው ቀርቦ ከሰአታት እሰጣ እገባ በኋላ ኮሚኒቲው ስብሰባውን ለመጥራት ቢያንስ ከአስር ያላነሱ ወላጆችን ፊርማ ይዛችሁልን ቅረቡ ሲል ጥያቄ አቀረበና ይህም አስር የተባለው ፊርማ በአንድ ጀንበር ከ70 በላይ ወላጆች ፊርማቸውን አስቀመጡበት፡፡ ፊርማውን በማሰባሰቡ አጋጣሚ ከሁሉም በላይ እንደአሸን የፈሉት የመንግስት ፖለቲካ ፓርቲ አባላት በኩል ተቃውሞ እንዳይነሳ ፍርሃት ነግሶ ነበር፡፡ ያም ሆኖ የተከሰተው ከዚህ የተለየ ነበር፡፡ የወላጅ ኮሚቴውን መቋቋምና የትምህርት ጥራቱን እያደረ መዝቀጥ የድርጂት አባላቱ አቀንቃኞች የሚቃወሙት ሆኖ ሁላችንንም አስደሰተን፡፡ ይህም ሂደቱን አልጋ በአልጋ አደረገው፡፡ ይህ የፊርማ ማሰባሰብንም የወላጁን ስሜት በጥልቀት እንድረዳ ረድቶኛል፡፡ ትምህርት ቤቱ እንዲሰሩልን በኮሚኒቲውና በቆንስሉ በኩል ሸህ ሁሴን አል አሙዲ ለአመታት ሲለምኑ ቢከርምም ሳይሳካ መቅረቱ እንዳለ ሆኖ ሌላ ቢያግባቡት ሌላ ተአምር መፍጠር የሚችለውን ወላጅ ፈንግለን ስሜቱን አድምጦ ማሰባሰብ ባለማቻሉ ሸህ አል አሙዲን አንጋጠን ስንጠብቅ በወላጁ ሊሰራ የሚችለውን ስራ ለማየት አልታደልንም. . . ለዚህም ራሴን ጭምር ወቀስኩ ! " ድር ቢያድር አንበሳ ያስር ..." እንዲሉ ብሶት የወለደው ህብረት የፈጠረለትን ወላጅ የሃይል ሚዛን ስመለከት የኮሚኒቲም ሆነ የመንግስት ተወካዮቻችን በልመና ሲባዝኑ ያላስተዋሉት ሃብት በእጃቸው እንደነበር ከተረዳሁት ቆየት ቢልም የአሁኑ ግን ልዩ ስሜትና ቁጭት ፈጠረብኝ !

ቀኑ ደረሰ ... የወላጁ ጥሪ በትምህርት ቤቱ በተበተነ ማስታዎቂያና በተንቀሳቃሺ ስልክ በኩል በስርአት ተላለፈ፡፡ እኔም ጥሪ ከደረሳቸው ወላጆች ጋር በስብሰባው ላይ ተገኘሁ፡፡ የጎመራው ትምህርት ማዕከል ተስፋ አድጋ ላይ ነው መባሉ ያሳሰበው ወላጂ ታይቶ በማይታወቅ መንገድ አዳራሹን ከአፍ እስከ ደገፉ ሞልቶታል፡፡ በመንግስት የፖለቲካ ድርጂቶችና በልማት ማህበራት ድግስና ስብሰባ የተሰላቸው ወላጅ አዳራሹ አጨናነቀው፡፡ ወንበር ጠፋ...የጎመራው ተስፋ እንዳይጠዎልግ የሚፈልግ ሰራዊት መሆኑን ልቤ ታወቀውና ደስታ ተሰማኝ...በወንድም እህቶቸ ኩራት ተሰማኝ ... በወገኔ ኮራሁ ! ስብሰባው እንደተጀመረ ስብሰባውን ጠሪ ወላጆች መድረክ ላይ ወጥተው ሃሳባቸውን እንዳይገልጹ ቢገደቡም ጉዳዩን ሳያነሱ የከረሙት የኮሚኒቲ ባለስልጣናት ስብሰባው ከፈቱት ! ስብሰባው በሰላማዊ መንገድ እስከተካሄደ ድረስ "ምን ገዶን" የሚሉት ስብሰባውን ጠሪ ወላጆች ስጋታቸው ግርግርና መጠላለፍ እንዳይነሳ እንጂ በወንበር መቀመጥ አልነበረምና በዝምታ አለፉት፡፡ ያም ሆኖ ስብሰባው በስጋት ቢቀጥልም በስርአት ቀጠለ፡፡ ወላጂ ጎደለብኝን የሚለውን ማቅረብ ጀምሮ ስብሰባው ጤነኛ በሆነ መንገድ ቢቀጥልም ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ እንዳይዎጡ የሚገድቡ ሁኔታወች የሉም፡፡ የወላጁ ጥያቄ ሰብሰብ ብሎ ሊቀርብ አለመቻሉ ሌላ የአካሄድ ችግር ፈጠረ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ አቅጣጫውን የተረዱት መድረክ የተነፈጋቸው ጊዜያዊ የወላጅ አስተባባሪ ወላጆች ስብሰባውን በስርአት ለማስኬድ ይቻል ዘንድ ሃሳባቸውን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ጠየቁና ተፈቅዶላቸው ጥያቄያቸውን አቀረቡ ... እንዲህ ይላል ... ! " በሳውዲ አረቢያ ለምንገኝ ኢትዮጵያውያን የራሳችን አለም አቀፍ ትምህርት ቤት መመስረትና ካለፉት በርካታ አመታት ወዲህ ልጆቻችን የሃገራችን ባህልና ቋንቋ አውቀው የሚማሩበት የትምህርት ማዕከል እንዲሆን ላበቃን ፈጣሪ ምስጋና ይግባው ! ይህም የሩቅ ህልማችን የሰመረበት ታሪካዊ ክንውን በመሆን ታላቁ የስኬት

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ምዕራፍ መግለጫ ነው ማለት እንችላለን ! በጣት በሚቆጠሩ ተማሪዎችን ይዞ በኮንቴነር የተጀመረው መማር ማስተማር ዛሬ ተበረታቶና በሽዎች የሚቆጠሩ ልጆቻችን ትምህርት ማስቀሰም በቀጠለበት በዚህ የታሪክ አጋጣሚ ህልማችን እውን ላደረጉልን የመንግስት ተወካዮች፤ ተመራጮች፤ ተባባሪዎችና ሃገር ወዳድ ግለሰቦች በግል ሳይቀር ለተከፈለው ታላቅ መስዋዕትነት ነዋሪው ታላቅ አክብሮት አለው! ዛሬ ሁላችንም የምንኮራበት ትምህርት ቤት አለን፡፡ ያም ሆኖ በአስራ አምስት አመት ጉዟችን ራሳችን የምናዝበት የራሳችን የሆነ የትምህርት ቤት ህንጻ ግን የለንም፡፡ ይህ ባለመሆኑ ለትምህርት ቤት ኪራይ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እናዎጣ ዘንድ ተገደናል፡፡ ይህ መቀጠል የለበትም፡፡ ይህን ከፍተኛ ወጭ ለመገድብ ብቸኛው አማራጭ ትምህርት ቤት መግዛት ብቻ ነው. . . ወደድንም ጠላንም ከፍተኛ ወጭያችን ለመቀነስ ይህ መሳካት የሚገባው መሰረታዊ ህልም ነውና ለስኬቱ ከኛ ብዙ መጠበቁ ሳይታለም የተፈታ ሃቅ ነው፡፡ ይህንን ለማሳካትና እንደ ዜጋ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግና ማጎልበት የውዴታ ግዴታችን ነው፡፡

" ዛሬ የመማር ማስተማሩ አድማስ ሰፍቷል፡፡ የተማሪዎች ቁጥር ከአስሮች ወደ ሺዎች ተሸጋግሯል፡፡ ይህ በሆነበት መልካም አጋጣሚ ግን በተማሪዎችና በትምህርት ቤቱ በኩል ድልድይ መሆን የሚገባን ወላጆች እንቅስቃሴ ጉልህ ሆኖ አይስተዋልም፡፡ በወላጆች ጥያቄ የተጠራው ይህ ስብሰባ ዋና አላማም ወላጆችና ለትምህርት ቤቱ መጠናከር ስለሚኖራቸው አስተዋጾ፤ በትምህርት አሰጣጡ ዙሪያ ወላጆች በሚያሰሙዋቸው ቅሬታዎችና ከወላጁስ ምን ይጠበቃል በሚሉት አንኳር ነጥቦች ዙሪያ መመካከር ይሆናል፡፡ ..." የሚለው መሪ ቃል ሆኖ ስብሰባው በተረጋጋ መንፈስ ተከወነ ... ስጋት የወለደው የስደተኛ ወላጆች ህበረት ዛሬ በድል ተደመደመ ! እሰየው ... !

የአረብ ሃገራት ስደትና ስደተኞች ወግ ሲነሳ ሁሉም በአዕምሮው የሚስበው የስደተኛው መከራ ችግርና ሰቆቃው እንጂ ደግ ደጉ አለመሆኑ ብዙም አይደንቀኝም፡፡ በእርግጥም በሃበሻው ህይዎት ዙሪያ የሚታየው ችግሩ ሰፋና ገዘፈ ሲባል ለዚህ ሁሉ የዳረገን ምንድን ነው? ብሎ መጠየቁ አግባብነት አለው፡፡ በዚህ ዙሪያ ግንዛቤን አገኝ ዘንድ የስራ ጸባየ ፈቅዶ በችግሩ ዙሪያ በተለያዩ ሃገራት የሚገኙ ዳፋ ቀማሾችንና የመንግስት ተወካዮችን የማነጋገር እድል አግኝቻለሁ፡፡ ከሰበሰብኳቸው መረጃወች መካከል በጅዳና አካባቢዋ የሚገኙ ህጋዊ ነዋሪዎችን በማህበር ለማደራጀት ከኢትዮጵያ የመጡ አንድ ከፍተኛ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ባለስልጣንን በጉዳዩ ዙሪያ አነጋግሬያቸው የሰጡኝ ምላሽ ሁሌም ከህሊናየ አይጠፋም፡፡ ጥያቄየ አንድና አንድ ነበር፡፡ ይህውም በሳውዲ አረቢያ ከመቶ ሺዎች በላይ ስደተኞች ይገኛሉ ይህ ከግምት ገብቶ ውጭ ጉዳይ የዜጎችን መብት ለማስከበት ለምን በቂ ዲፕሎማቶች አይመደቡም? በሚላኩት ጥቂት ዲፕሎማቶች በቂ ልምድን ፤በቂ የቋንቋ ክህሎትን የተካኑ መሆናቸው ተገምግሞና ተመርጠው የማይላኩት ምክንያቱ ምንድን ነው? መረን የለቀቀውን የስደተኛውን ችግር ለመግታት መንግስት ምን እያደረገ ነው? መፍትሄውስ ምንድን ነው ይላሉ? በማለት የጭንቀቴን ያህል ጥያቄወችን መመጠን ተስኖኝ ጠየቅኳቸው ... ወንድሜ ችግሬ ገብቷቸው ትንሺ እንደመተከዝ ብለው ገብስማ ጸጉራቸውን እያሻሹ ሲመልሱ እንዲህ አሉኝ "... ወንድሜ ጥያቄህና ችግሩ ይገባኛል፡፡ መልስ ቢኖረኝም አንተን ቀርቶ መልሱ እኔን እንደማያጠግብበኝ አውቀዋለሁና ብዙ ማለት አልፈልግም፡፡ በተለይም ወደ አረብ ሃገራት የሚላኩ ዲፕሎማቶችን በሚመለከት ያለውን ችግር የምጋራው ቢሆንም እንኳንስ የአረብኛ የሚናገሩና ባህሉን ተዋህደው የሚሰሩ ዲፕሎማቶች ቀርቶ በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በቂ ልምድ ያላቸውን ለማግኘት ያለውን የተማረ ዜጋ እጥረት የምንረዳው በጉዳዩ ውስጥ ያለን

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ብቻ ነን፡፡ በአጠቃላይ የተማረ ሰው ችግር አለብን፡፡ ችግሩ እንዴት ይቀረፋል ካልከኝ ለአጭር ጊዜ ብቸኛው መፍትሄ መጀመር ካለበት የሚጀምረው በአካባቢው የምትገኙ ነዋሪዎች በኮሚኒቲ ስር ተጠናክራችሁ በመደራጀት ብቻ ነው፡፡ በረጅሙ መመልከት ትልም አድርጋችሁ መስራት ያለባችሁ ግን የከፈታችሁትን የኢትዮጵያውያን ት/ቤት ማጠናከርና ብቁ ዜጋን ማፍራት ነው፡፡ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ወደ አረብ ሃገራትን የሚላኩ ዲፕሎማትና ለማግኘት ለዘመናት የሚታየውን ችግር ለመፍታት ብቸኛ መፍትሄ ይህ ጅምር ይመስለኛል፡፡ ልጆቻችሁን ዛሬ በሃገራቸው ቋንቋ የምታስተምሩበት ት/ቤት ከፍታችሁዋል፡፡ ትምህርት ቤቱ ጊዜያዊውን በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ችግር አይፈታውም፡፡ ያም ሆኖ በዘላቂነት ችግራችን ሆኖ የኖረውን ከአረቡ አለም ጋር የሚያስተሳስሩን ዲፕሎማቶችን የማፍራቱ ትልቅ ተስፋ የሚጣልበት እንደሆነ ልገልጽልህ ግን ግድ ይለኛል፡፡ ለኔ በኮሚኒቲ ስር ተጠናክራችሁ በመደራጀት ይህን መሰል ተስፋ ብታጎለብቱ እንጂ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኩል አንጋጣችሁ መፍትሄ ብትፈልጉ "ላም አለኝ በሰማይ ..." ነው የሚሆነው... " ሲሉ ልክ የዛሬ አስራ አንድ አመት ገደማ ነበር የነገሩኝ፡፡ ችግሩ እንደዛሬው ሳይገዝፍ እንደዜጋ ባዩት በሰሙት አዝነውና ተከዘው የመለሱልኝ አይረሳኝም፡፡ ወንድሜ በምስረታው መባቻ ዳዬ የሚለውን የኢትዮጵያውያን አለም አቀፍ ትምህርት ቤት ጎብኝተው ያሳደረባቸውን ተስፋ አይናቸው እንባ እያቃረ እንዳጫዎቱኝም የምዘነጋው አይደለም፡፡ ወንድሜ ያሉት ትክክል ነበር፡፡ ከአስራ አንድ አመታት በኋላ የነዋሪው ችግር መግዘፉን መካድ አይቻልም፡፡ ይህም ሆኖ ችግራቸን ገፍተን በምናስተምራቸው ልጆቻችንና ትምህርት ቤት ዙሪያ ጎምርቶ እያየነው ያለው ተስፋ እንዳይጠወልግ መንግስትና የሚመለከታቸው ሁሉ ከምንግዜውም በላይ ድጋፍ ሊያደሩ ይገባል ! ጀሮ ያለው ሊሰማ ይገባል ! ከዚሁ ጎን ለጎን ወላጆች በአዲስ መልክ ከመሰረቱት የወላጅ ኮሚቴና ከትምህርት ቤቱ ጎን በመቆም ለተጀመረው መልካም ተንሳሺነት ድጋፍ ሊሰጡና የመማር ማስተማሩን ህልም ከስኬት የማድረስ ታሪካዊ ግዴታን ሊወጡ ይገባል፡፡

ዘንድሮ ጊዜ ወርቅ ነው አሉ. . . ይህችን መጣጥፌን ለማንበብ ለሰጣችሁኝ ጊዜ አመስግኜ ልለያችሁ ... ! ይቀጥላል . . .

የነገ ሰው ይበለን !

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!